# ከጠላፊ ስለ ጠላፊ

ኢያሱ ዓለማየሁ

አርባ አምስት ዓመታት በትግል አልፈዋል፣

ተነሱ ያለን ችግር አልሄድ ብሎ ባጅቷል፣

እንኳን አይሮጵላን ሰውም ይጠለፋል።

ዘመን ተለውጧል። ጊዜው ሄዷል። የኢትዮጵያ የፍትህና ዴሞክራሲ ጥም ግን ዛሬም አለና እኛ ወጣት ተማሪዎች (ከ19 እስከ 27 ዓመት ውስጥ የነበርን) የዛሬ 45 ዓመት ነሐሴ 1961 አይሮጵላን ጠልፈን ሱዳን ስንገባ ከያኔ የእኛ ዕድሜ ባይበልጥም (31 ዓመት) ሀይለ መድህን አበራ ደግሞ ባለፈው ሰሞን ጠልፎ ወደ ጀኔቫ ገብቷል። እኛ በዘመኑ ባይናቅም (አንድ የስርአቱ ደጋፊ ሲያከቸለችል ዕንቁላል የጫነ ብሎታል) የጠለፍነው ዲስ 3 ከጎንደር በባሕር ዳር አድርጎ ወደ አዲስ አበባ የሚሄደውን ነበር። ሀይለመድህን ደግሞ ዘመናዊን ቦይንግ የጠለፈ ሲሆን የዚሁ አይሮጵላን ረዳት አብራሪነቱ ተነግሯል። ለምሳሌ እኔ አይሮጵላን ላይ የወጣሁት ለመጀመሪያ ለጠለፋው ጊዜ ነበር። ሀይለ መድህን በስልት ጠልፎና ጠባቂዎች እንዳይገድሉት በመስኮት በገመድ የወጣ ሲሆን እኛ (7 ነበርን) አንድ ጥይት ያለው ሽጉጥና አንድ እጀታው በዝሆን ቀንድ የተሰራ ሳንጃ (የአባቴን) ይዘን አብራሪዎቹን አስፈራርተን ድርጊቱን የፈጸምን ነበር። ከዚያን ከ1961 በኋላ ሌሎች ጠለፋዎች ሞክረው የተሳከላቸውና የከሸፈባቸውና የሕይወት ዋጋን የከፈሉም (በጥይት የተገድሉም እንደነ ማርታንና ዋለልኝ ወይም የታረዱ ሌሌች) ነበሩ።

በበኩሌ ወደ ጀኔቫ ጠለፈ የተባለውን ዜጋ አላውቀውም። ወያኔ ግን እብድ ወይም በሽተኛ ሊለው እየጣረ ስለሆነ ድርጊቱ እንዳጋለጣቸውና እንዳበገናቸው መገመት ችያለሁ። እኛንም የአጼው መንግስት በትምህርታቸው ደካማና ፈተና የወደቁ ብሎን እንደነበር አስታውሳለሁ። በሱዳን ለ6 ወር ሲያሳስሩንምና መልሱልን ብለው የጨቀጨቁት አልሳካ ሲል አስወጡልን ብለው አለ ፍቃዳችን በፖሊስ ታጅበን (የሱዳን፤ ግብጽ) ወደ አልጄሪያ ተወስደን ተጥለን ነበር። ሀይለ መድህንም ለረጅም እስር እንዳይዳረግ የተጀመረው ጥረት ተጠናክሮ መቀጠል አለበት። እኛ በጠለፋ የተሰማራነው አንድም የተማሪዎን ትግል በዓለም አቀፍ ደረጃ እውቅና ለማሰጠትና በዚያውም ወደ ሱዳን ወጥቶ ትጥቅ ትግልን ለማደራጀት ሲሆን የሀይለ መድህንም ጠለፋ (በስዊስ የአየር ክልል ስላልተደረገ ስዊስ በጠለፋ ልትከሰውም አይገባም) የወያኔን አገዛዝ በሰፊው አጋልጦታል። ይባርክህ፤ ተከታዮች ይኑርህ፤ በርታ ይባላል እንጂ አንዳንዶች --ያውም የወያኔ ተቃዋሚ ነን እያሉ--ጠለፋው እንኳን መጥፎ ድርጊት ነው ሊሉ መነሳታቸው ምን ያህል የፖለቲካ ብስለት እንደራቀን

የሚያሳይ ሆኖ አግኝቸዋለሁ። ወያኔን በሁሉ መስክ በሁሉ መንገድ መታገል ሲገባ የወያኔ ጡት አባቶች ለይስሙላቸውና የማይመቿቸውን አሸባሪ የሚሉትን ተቀብሎ በአሜሪካ ቡራኬና መስመር ብቻ ትግል ለማካሄድ መፈለግ በጣም ሞኝነት ነው። አሜሪካ የራሱን ብሔራዊ ጥቅም ሲያስጠብቅ ጠበቅ ያለ ምርመራ ብሎ የለየለትን ስየል ይፈጽማል፡፡ ከወደ ሰማይም አጥፊ ቦምቦቹን እየወረወረ የሰው ቁጥር ቅነሳ ዘመቻውን ቀጥሎብናል። በ አጭሩ የሚፈልገውን ለማግኘት ሀይል ይጠቀማል፤ ይጥራል፣ ያሰቃያልና ስለ ሰላማዊ ትግል ቅንጣትም ሊያስተምር ሊመክር የሚችል አይደለም። ወደ ሮማ ሳይሆን ወደ ጀኔቫ የበረረው ሀይለ መድህን ወያኔ ሊያጠቃኝ ሊያጠፋኝ ነው ብዬ ሰግቼ ነው፤ የሰብዓዊ መብት ረገጣ የወያኔ መለያው ነው እስካለ ድረስ ወያኔን ዴሞክራት ወዘተ እያሉ የሚያቅራሩትን ሁሉ አሳፍሮልናል። ዛሬ የሚያስፈልጉን ዜጎች በዘረኛው አገዛዝ ላይ “አብደው ተናደው” የሚያምጹት እንጂ እርቅና ሰላም ሊሰብኩ ወይም ከወያኔ ሊተቃቀፉ የሚከጅሉት ሊሆኑ አይችሉም። ጠላፊዎች፤ አፈንጂዎች፤ ተኳሾች፤ “ያበዱ ያከረሩ” አማጽያን ያስፈልጋሉ። ሌላው ሁሉ ከንቱ ነው--ወሬ ሊጎዳ ቢችልም ተግባር ከጠፋ አገዛዝን በራሱ አይጥልም። የህዝብ አመጽና ትግል ያስፈልጋል። ጠለፋም የዚሁ ሰፊና ባለ ብዙ ፈርጅ ጸረ ወያኔ ትግል አንዱ ክፍል ነውና ሊበረታታ ሊመሰገን የሚገባው ድርጊት ነው።

ወደ መመጻደቅ አይወሰድና ጠለፋ ድፍረትን የሚጠይቅ ነው። ብዙ ዜጋ በሰላማዊ ሰልፍ ላይ በሚጠበቀው ደረጃ የማይገኘውም ምክንያቱ ግልጽ ነው። ትግል ግን አርአያ የሚሆኑ ሊሞቱ ዝግጁ የሆኑ ያስፈልጉታል። የተማሪዎች ትግል አርአያ የሆኑና ተከተሉን የሚሉ ጀግኖች ነበሩት-- የነ በረከተ መርገም፡ ድህው ይናገራል ገጣሚዎችና ተገራፊዎች። የታህሳስ መፈንቅለ መንግስት ሞካሪዎች--ዛሬ ጥራዝ ነጠቆች ግርግር የሚሉትን ታሪካዊ የመፈንቅለ መንግስት ሙከራ ያደረጉት። አጼውን ሊሾፍ የሞከሩት እነ ደጃዝማች ታከለ ወልደ ሐዋርያት፤ በግፍ የተገደሉት እነ ጥላሁን ግዛው ወዘት። የየካቲቱማ አይነሳ! በዘመነ ደርግ የነ ሞት አይፈሬዎች ትግልማ ስንቱን ባስተማረ ነበር ዛሬ ወያኔና ተምቾቹ በሀገር ፈልተው ያንን ትውልድ ባያጠቁና ስንቱን ባያደናግሩ ኖሮ! ስለ ትግል ሀ ፐ ማለቱ ቢያስፈልግም እንኳን ማለቱ ምናልባትም መታበይን ሊያመለክት ይችላል ለሚሉ ያመች ይሆን በሚል ስጋት ዝምታ ቢመረጥም ካሳለፍነው ተመክሮና አሁንም ጠላፊው ወይም የአይሮጵላን አቅጣጫ አስቀያሪው እንዳሳየው ሞት ካልተደፈረ ውጤታማ ትግል ማካሄድ ይከብዳል። የቆየ ታሪክም ከጠቀመ እኛም በሌላ ሁኔታና ጊዜ አይሮጵላን ስንጠልፍ ወይም ከጎንደር አዲስ አበባ ቲኬት ገዝተን ግን ከባሕር ዳር ወደ ካርቱም ስንበር ካነሳናቸው ጉዳዮች አንዱ አብራሪው እምቢ ቢለንስ የሚለውን ነበር። ለነገሩ ዋናው አብራሪ ካርቱም መሄጃ ቤንዚን የለኝም ሲለን (በረሓ ላይ ታሳርፈናለህ ነው ያልነው) ወይም ለካርቱም ካርታ የለኝም ሲለን (አባይን ተከተል አልነው እንጂ) በምንም አይነት አንመለሳትም እንሞታለን ብለውን ወስነን ነበር የተሳፈርነው። ለውሳኔና አቅዋም ወይም ድርጊት አንደምታና መጨረሻውን አውቆ ከወዲሁ ቆርጦ መነሳት ያስፈልጋል። ይህ ቁርጠኛነት በጎደለበት ደግሞ ጠላት ሲያጓራ መፍረክረክና

እጅ መስጠት፤ የሕዝብን አድማ ማክሸፍ ወዘተ ይከተላል። ከወያኔ የበሸቀጠ ሸበጥ ስር ሊወድቁ የሞከሩትና አሁንም እየተሰናዱ ያሉት የቆራጥ ትግል ምሳሌዎች አልነበሩም/አይደሉምም። የሀይለ መድህን ድርጊት--ነገን ለነገ ትተን-- የሚመሰገነው ሞት ቢመጣም፡ እስር ቢከተልም ምናባቱ ብሎ ስለወሰነ ነው። አሊያማ የረዳት ፓይለት የግል ኑሮ ከበረንዳ አዳሪው የሚወዳደር ሆኖ አይደለም። የመጣ ይምጣ ብለው ሰልፍ የያደረጉትና እያደረጉም ያሉ ሙስሊም ዜጎች፤ በአዲስ አበባ በጎንደርና ባህር ዳር ሰልፍ የሞከሩት ዜጎች ሁሉ የሚጠበቀውንና ሕዝባዊ አመጽን የሚያጅበውን ድፍረትና ቆራጥነት ያሳዩ ናቸው። ለተጨባጭ አደጋ የተጋለጡት የሀገር ቤትን ዜጎች ምሳሌ በውጭ ሀገር ያለው ዜጋ ሊከተል ይገባዋል። በአጼው ዘመን ተቃዋሚ ተማሪዎች ኤምባሲዎችን ወረው ሲይዙና ይህ ነው የማይባል የፕሮፕጋንዳ ድል ሲያስመዘግቡ የምናሰታውስ በሕይወት አለን። ለዚህም ነው ጠለቅ ብለን ጉዳዩን ካየነው ጠለፋን እንኳ አንደግፍም ባዮች ማፈሪያዎች ሆነው የምናገኛቸው። ለሀይለ መድህን ሙሉ ድጋፍን መስጠትና ወደ እስር እንዳይዳረግ መጣር የዜግነት ግዳጃችን ነው። በሰራውና ባስገኘው ጸረ ወያኔ ውጤት። ለሎችንም ጥለፉ፣ ወያኔን አጋልጡ ነው መሆን ያለበት የሀቀኛ ሀገር ወዳድ ምክር። ሀገርና ጨቋኝ አገዛዝን አንድ ማድረግ ከፉ ስህተት መሆኑ መገንዘብ አለብን።

ዘመን ላስቆጠረ ያውም ለዲሲ 3 ጠለፋ ማውሳቱ ምን ይፈይዳል ለሚሉት ደግሞ ያም በጊዜው የነበረው አንደምታ ከፍተኛ ነበርና የአሁኑኑም ሆነ ቀጣይ ጸረ ወያኔ ሙከራዎችን በተገቢው መንገድና ሚዛን ማየቱ ተገቢ ነው ለማለት ነው። ወደ ጀኔቫ ጠለፈ የተባለው ቆራጥ ዜጋ የሚጠብቀው ምቹ አልጋ ሳይሆን መከራ መሆኑን ሳይገምት አልመጣም። ግን ቆርጦ የመጣው ይምጣ ብሎ በወሰደው እርምጃ ወያኔን ከብዙ በራሪ ወረቀቶችና ስብሰባዎች በበለጠ አጋልጧል። ከእለታት አንድ ቀን ያኔ ድሮ ቦይንግ በሀገር ውስጥ በረራ ባልነበረበት ጠለፋ አካሂደን ነበርና አይዞህ በርታ ማሰማቱ ይገባል በሚል ነው ይችን አጭር መልዕክት የጻፍኩት። እኛም ጠላፊ ተብለን ታስረናል፤ ጠላፊ ተብለን የስደተኛ ወረቀት ተከልክለናል (አንዳንዶቻችን እስከ 1996 በፈረንጆች አቆጣጠር፤ በሀሰት ሰነድ መዳጋዝ ተገደናል) ወዘተ… ግን በወሰድነው እርምጃ ተጸጽተንም አናውቅም። ሀይለ መድህንም የመጣ ቢመጣ መቻልና መቋቋም አለበት። ዜጎች ደግሞ ዘመን ተቀይሮ በተለይ በባዕድ ሀገር መቃወምም የሚቻልበት ጊዜ ነውና ሊታደጉት፤ ሊከላከሉለት ያስፈልጋል። ከድሮ ጠላፊ ለአዲስ ጠላፊ ያለኝ መልዕክት ምስጋናና አይዞህ በርታ ከጎንህ አለን የሚል ነው።